2158. ኬታወ ዘሬ ዴሬቀስ

. በባለቤቱ ላይ እንሽላሊት ያፈጥበታል

.. በገዛ ዳቦዬ ልብ ልቡን አጣሁት

2159. ኬታወይ ዴእሽን እመተይ ሣሼስ

. ባለቤት እያለ እንግዳው ያስተናግዳል

.. ምኝ ቤት እንግዳ ይናኝ

.. የባለቤት ሰነፍ ቤቱን ያዋርዳል

2160. ኬታው ኪርያረ ሚሽን ተ ኣቡ አውን ከዎትዼ!

. ባለቤቱ በወጪት ሲበላ እኔስ አባቴ የት ነገሰ!

. እንዳገሩ ይኑሩ እንደወንዙ ይሻገሩ

2161. ኬታይያ ኬታዋ ቆሃይሲ ጋደ ባሪገን ምታ ዬደውሱ

. ሴትየዋ ባልዋን የጉዳች መስሏት በእንትድ ውስጥ እንጨት ትሰዳለች

.. ባልዋን እጉዳ ብላ እንጨት ሰደደችበት

2162. ኬት ኪህን ዴሽያ ዎንዘውሱ

. ቤት ሲመች ፍየል ታግታለች

.. ከቤት ዶሮ ሲታረድ ከደጅ ቆቅ ይያዛል

2163. ኪጥድ ክይደ ነአይ ሾሮ፣ ኩሼፔ ክይደ ሚሽ አሜ

. ቤት ሰርቶ ጉጆ የወጣ ልጅ ጉረቤት ነው፣ ከእጅ የወጣ ገንዘብ እዳ ነው

.. ብርሌ ከነቃ አይሆንም እቃ

2164. ኮሌ ዘልእን ኮሌ ዎዴስ

. ባለአንድ ፍሬ ቢነግዱ ሌላ ባለአንድ ፍሬ ይተርፋል

.. ውሃ ቢወቅጡት እምቦጭ

2165. ኮሌይ ሶን ኦርዴስ

. ሙክት እቤት ይሰባል

.. ለሁሉም ቦታና ጊዜ አለው

.. ከአነጋገር ይፈረዳል ከአያያዝ ይቀደዳል

2166. ኮርመይ ሰንግሳ ላጩስ፣ ትያ በርሳጋ ቀይጩስ

. ወይፈን የቀጠቀጠውን ይልሳል፣ እሸት ያጐረሰውን ይወጋል

.. ብር ላበደር ጠጠር

2167. ኮሶይ (ሶይዶይ) ምን መልአየ! ቢታ ጉጃ

. ኮሶ ዱሮስ ይጣፍጣልን? አፈር ጨምርበት

.. ወደሽን ገጣቢት ንጉስ የምታመሰግኚ

2168. ኮሸ ለይት ቀጠራ ጌልዳጌ ሀለይተፔ ከሎይ ባወ ጌስ

. በረሃብ ዘመን የተገረዘ ከዘንድሮ የበለጠ ጥጋብ የለም ይላል

.. በፋሲካ የተቀጠረች ገረድ ሁልጊዜ ፋሲካ ይመስላታል

2169. ኮሸይ አይክድ በሺያፔ ፖንሲስ ሳሞይ አይክድ ሸፍያፔ ኡሹስ

. ረሃብ ሲይዝ ከምጣድ ላይ ያስቆነጥራል

. ጥም ሲይዝ ከደለል ላይ ያስጠጣል

.. የተቸገረ እርጉዝ ያገባል

2170. ኮሻፔ ዱሬ ሎኦ

. ከረሃብ ሀብታምነት ይሻላል

.. ቢያስቀዝንም ጮማ ይሻላል

2171. ኮሼነ ኮከይ ፖሼነን ከኤስ

. የማያስፈልግ ንፍሮ ሣይፈለፈል ይበስላል

.. የፈሩት ይደርሳል የጠሉት ይወርሳል

2172. ኮባረ ዴእያበይ ፐላረ ዴእያባ ዩሌስ

. ግፍ ያለበት መአት ያለበትን ይወልዳል

. ያልዘሩት አይበቅልም

2173. ኮንተ ከዎይ በው ቀሹዋን ዴኤስሽን አሰው ዋስያ ጌሌስ

. የኮንታ ባላባት ለራሱ ከአስር ቤት ሣይወጣ ለሌላው ዋስ ይሆናል

.. አንቃ ለራሱ አይበቃ ለሰው ጠበቃ

2174. ኮንተ ኮሌ ብረሰነ ቢድ ብረሴትድ ዩስ

. የኮንታ ወጠጤ ሊሰር ሄዶ ተሰርሮ ይመለሳል

.. እሰራለሁ ብላ ሄዳ ተላጭታ መጣች

2175. ኮካ ከሎይ መሽኳ ዱትሴስ

. የንፍሮ ጥጋብ ሽርጥ ያስበጥሳል

.. የጠገበ ሰው ራሱን አያውቅም

2176. ኮከይ ኡየና ሃታ ዮረይ ኡዩስ

. ንፍሮ የሚጠጣውን ውሀ ስስታም ይጠጣል

.. ሆዳም ሰው ፍቅር አያውቅም

2177. ኮይሮ ሹሃስ ቦንጎዮ ዶርስያ ሀች ሰሎ ቤኣስ ገውሱ

. ሊያርዱ ያዘጋጇት በግ ዛሬ ሰማይ አየሁ ትላለች

.. ያላወቁ አለቁ

2178. ኮይሮ ክይደ ሀይተይ ዲሽን ጉዩፔ ክይደ ከጬ ከንቴስ (ጦኔስ)

. ፊት የወጣ ጆሮ እያለ ከኋላ የወጣ ቀንድ ይበልጣል

.. ፊት የወጣን ጆሮ ኋላ የበቀለ ቀንድ በለጠው

2179. ኮይሮ ኬሶ አሰራ! ኮምፑዋረ ኡስቶ ማታ (ጠማታ)

. መጀመሪያ የቆረጡት ያንገት ልብስ (ሽርጥ) ከሽልጦ ጋር ያማጉት ትኩስ ወተት

.. እጅ ለአፍ ሚዛኑ ነው

2180. ኮይሮ ግያ ጌልየ ከነይ ጌዳ ጎቼስ

. መጀመሪያ ገበያ የሄደ ውሻ ወርች ይጐትታል

.. ማወቅ መላቅ አለማወቅ መናቅ

2181. ኮይሸ ኮሱዋ ኮራኔ፣ አበለ ጠድያ ሎሃኔ፣ ዴንጎ ዶርሰ
ጩላኔ ፐራ ዞኮይ ገቴስ

. የኮይሻን የኮሶ እንጨት ኮርቻ፣ የአባላን (ባህር) ጉማሬ መሳቢያ ለኮ፣ የደንጐን የበግ ደበሎ የፈረስ ጀርባ ያገናኛል

.. የሺ ፍልጥ ማሰሪያው ልጥ

.. ፃድቃን ሣይቀጣጠሩ ይገናኛሉ

2182. ኮጥያ ኮይሽን ኦለይ ቤቴስ

. መቆፈሪያ (አንካሴ) ሲፈልጉ የተቆፈረ ጉድጓድ ይገኛል

.. በድንገት አህያ ከጅብ ቤት

## ወ

2183. ወለከ ወለከ ግሸ ግን ጌዲያ ዬዴስ

. እየደባለቅህ አድል ቢሉት እግሩን ይሰዳል

.. ሞኝ እንደመከሩት

2184. ወራ ኤሬን ኡረይ አይፌ ቶይሲስ

. አመታት የማያውቅ ሰው አይን ያጠፋል

.. የሞኝ በትር ሆድ ይቀትር

2185. ወከለይ ቆልአ ጌልድ ደዌ ግዴስ

. እባብ ጓዳ ገብቶ ዘንዶ ይሆናል

.. ባጐረስኩ እጄን ተነከስኩ

2186. ወከለይ አውሶ ጌልድ ደዌ ግዴስ

. እባብ ሰው ቤት ገብቶ ዘንዶ ይሆናል

.. ያልጠሩት ሰርገኛ በትረኛ

.. ባጐረስኩ ኢጄን ተነከስኩ

2187. ወከል ጐሜ አዴሶ ጌልድ ደዌ ግዴስ

. እባብ ሀጢአተኛ ቤት ገብቶ ዘንዶ ይሆናል

.. ሥራ ለሰሪው እሾህ ላጣሪው

2188. ወራ ዶስየ ሌካይና ጌንዶን እራይ ዋዴስ.

. ድብደባ የሚወድ የሌካዮን ልጅ ጌንዶ ዝናብ ይደበድበዋል

.. ልማድ ከልጓም ይስባል

2189. ዋሰ ኡረይ ሶን አትን ዋሲን ክየ ኡረይ ከፋ ሣረዳ ጌሌስ

. የጮኸው እቤት ሲቀር ተጩሆ የወጣው ከፋ ሰራዳ ይገባል

.. ፊት የወጣውን ጆሮ ኋላ የበቀለው ቀንድ ይበልጠዋል

2190. ዋስ ኬሰ ኩቶይ ሶን አቲን ዋሲን ክየ ከነው ጒባ ጤራን ዎንቴስ

. ጮሆ ያስወጣ ዶሮ እቤት ሲቀር ዶሮ ጮሆ የወጣው ውሻ ጒባ አፋፍ ላይ ይነጋለታል

.. በፊት ከወጣ ጆሮ ኋላ የበቀለ ቀንድ በለጠ

2191. ዋስ ዴንተ ኩቶይ ሸኩዋን አትን፣ ዋሲን ዴንደ ጎደይ ጎፌ ጤረ ጌሌስ

. ጮሆ ያስነሣ ዶሮ ቆጥ ላይ ሲቀር፣ ዶሮ ጮሆ የተነሣው ባለቤት ጐፋ ጫፍ ይደርሳል

.. ፊት የበቀለ ጆሮ እያለ ኋላ የወጣ ቀንድ ይበልጣል

2192. ዋሴ በይነን እሞፐ፣ ሰአ አይሌነን ዜሮፐ

. ዋስ ሣይኖር አትስጥ፣ መሬቱን ሣታለሰልስ አትዝራ

.. ያልጠረጠረ ተመነጠረ

2193. ዋሶ ኤሬነ ከፍያ ውርቴ ገውሱ

. ጩሃ የማታውቅ ወፍ እለቁ ትላለች

.. እርሟን ብታፈላ ጋኑን ሙሉ አተላ

2194. ዋት ኬሰንዴ ጊዶ ሶይዱ አይፍያ ቶይሴስ

. እንዴት ያሸር ይሆን የተባለው ኮሶ አይን ያጠፋል

.. ያመኑት ፈረስ በደንደስ

2195. ዋን ጣገኔ ጊዶ ቦረይ ህምባ ጌስ

. እንዴት ያገሳ ይሆን የተባለው በሬ እምቧ ይላል

.. ያመኑት ፈረስ በደንደስ

2196. ዋንድ ዋሰኔ ጊዶ ቦረይ እስኖ ጣጌነን እጤስ

. እንዴት ይጮህ ይሆን ያሉት በሬ አንድ መጩህ ያቅተዋል

.. አስቀድሞ ማመስገን ለሀሜት ይቸግራል

2197. ዋኖ ግን ዋኖ ግየገን ገቶፖ

. ምን ልሁን ሲባል ምን ልሁን ከሚለው ጋር አያጋጥም

.. ችግር ሲያወሩ ችግር ከሚያወራ አይጣል

2198. ዋይ አይቅዶ ቦልያ ቄፍያረ ሜቴስ

. ተቸግሮ የያዙትን አንበጣ እስከነክንፉ ይበኋል

.. ሰርቶ ያገኙት ሀብት ያንገበግባል

2199. ዋይ ዴምዶ አዝና በአደ ጋጪውሱ

. በስንት ችግር የተገኘውን ባል አገላ ትፈጫለች

.. የተቸገረ እርጉዝ ያገባል

.. ያልጠረጠረ ተመነጠረ

2200. ውረነ መተይ ተማ ዱኪስ

. የሚያልቅ ንብ እሣት ይነድፋል

.. አለማረፍ የተርብ ቤት መቀስቀስ

.. አይጥ ሞቷን ስትሻ ስታበዛ ሩጫ፣ ሄዳ ታሸታለች የድመት አፍንጫ

2201. ውረነ አሰረው ውሬነ ዱልያ ቃሬቴስ ጌቴስ

. ለሚያልቅ ሸርጥ ሲባል የማያልቅ ቂጥ ይገልባል ይባላል

.. የማያዘልቅ ፀሎት ለቅስፈት

.. ትዝብት ነው ትርፉ

2202. ውረነ አሰረው ዴአነ ዱልያ ቃር ኡቴስ ጌቴስ

. ለሚያልቅ ሸርጥ ተብሎ የማያልቀውን ቂጥ ገልቦ ይቀመጣል ይባላል

.. የማያዛልቅ ፀሎት ለቅስፈት

.. ሞኝ የዕለቱን ብልህ ያመቱን

2203. ውረነ አሰረዮ ዴአና ዱልያ ቃሮጥ

. ለሚያልቅ ልብስ የሚኖር ቂጥ አትግለብ

.. ትዝብት ነው ትርፉ

.. የማያዛልቅ ፀሎት ለቅስፈት

2204. ውርስ ሃሰይዮጌኔ ምንት ደንጭዮጌ እሱዋ

. ጨርሶ የተናገረና ባጭር የታጠቀ አንድ ናቸው

.. ከአፍ ከወጣ አፋፍ

2205. ውርስ ማነይ ስንግ ስዩስ

. ጨርሶ የሚበላ በቅድሚያ ያሸታል

.. ሞኝ አያውቁብኝም ባይ

2206. ውርስ ማነይ ስንግ ጤሌስ

. ጨርሶ የሚበላ አሽቶ ያያል

.. ሞኝ አያውቁብኝም ባይ

2207. ውርስ አድን አጣሬ ኅፍንያ ቀንጤስ

. ጨርሰው ሲነግሩት ልኳንዳ አራጅ ሳምባ ይቆርጣል

.. ያመኑት ፈረስ በደንደስ

2208. ውሪን ሲቶገ ጡምን ዎጦገ

. ባለቀው አትቆጥብ በጨለማ አትሩጥ

.. ከወደቁ ወዲያ ወፈራገጥ ለመላላጥ

2209. ውቅ ኤርየይ ማላት ኀዜስ

. ስርቆት የሚያውቅ በምልክት ያስራል

.. እባብ ያየ በልጥ በረየ

.. ሌባ እናት ልጇን አታምንም

2210. ውቅ ኤርያጌ ጌድ ኤሬስ

. ሰርቆ የሚያውቅ ክትትል ያውቅበታል

.. ሌባ እናት ልጇን ቤት አታስጠብቅም

2211. ውቅዮይ ቀምበራሽን አይቅዮይ ግስትያ

. የሚሰርቀው አጃ ነበር የሚይዘው ስንዴ ነው

.. ስብ ያርዱ ጉፋያ ይነዱ

2212. ውቅደ ዎርዶይ ዴእሽን ሾሮ ጥሎይ ሀይቂስ

. የሰረቀ ውሸታም እያለ ሀቀኛ ጐረቤት ይሞታል

.. አይጥ በበላ ዳዋ ተመታ

2213. ውቄተይ አቴነሽን ጢርዮጋ፣ ለጌቴትዮጌ አቴነሽን ጌልዮጋ

. ከሰረቁ አይቀር መጥረግ፣ ከወሸሙ አይቀር መጋባት

.. ከለገሱ አይቀር ይንጋለሉ

2214. ዎለይ ዎዲድ ዎዲድ ሰአ ገኪስ

. ዋርካ ሴንገፈረገግ ቅርንጫፉ መሬት ይነካል

.. ቀስ በቀስ እንቁላል በእግሩ ይሄዳል

2215. ዎለይተ ቃለይ አማራ ጦኔስ

. ወላይትኛ ቋንቋ ለአማራ ያቅተዋል

.. ሸማ በየፈርጁ ይለበሳል

.. ካለባለቤቱ አይነድም እሣቱ

2216. ዎለይተን ሀይቆይ ሲቅዮ ሼሻ ደውሮን አሀይ ዎሬስ

. ወላይታ ሞት የሚወደውን ዘር ዳውሮ ሬሣ ይገለዋል

.. ላይቀር ሞቱ መንጠራራቱ

2217. ዎለይተይ የልዶ ዬሉዋ ማኒ ሃሰይዶ ቃላ ማናፔ ጌስ

. ወላይታ የወለድኩትን ልጅ እባላለሁ የተናገርኩትን ቃል ከምበላ ይላል

.. የተናገሩት ከሚጠፉ የወለዱት ይጥፉ

2218. ዎሉ ጠልያ ኡይን ባዳሲ ቱራ ማዩስ

. ዎሉ ኮሶ ጠጥቶ በዳሶ ሀረግ ይለብሳል

.. አቃቢት ኮሶ ጠጥተው ገበዙን ተጋረፈው

.. መልከኛው ኮሶ ጠጥቶ ጢሰኛው አሻረው

2219. ዎልቀይ በይነ የምባዲያ፣ አቾይ በይነ ሉሉምያ

. አቅም የሌለው ያጉበድዳል፣ ጥርስ የሌለው እንዲሁ ይውጣል (ያጉለጠልጣል)

.. አቅምን አውቆ መኖርን የመሰለ የለም

2220. ዎልቃመይ ዎርድ ዩሁዋ ድጌስ

. ጉልበታም ገድሎ ለቅሶ ይከለከላል

.. ጉልበት አለኝ የዝሆን አፍ አለኝ የመስፍን

2221. ዎልቃማቴ ፐልአነው መገነ

. ከጉልበተኛ ይልቅ ለጋሬጣ ያደገድጋሉ

.. ከኃይለኛም ኃይለኛ አለ

2222. ዎልቅ በይነ ኡረይ መሽኮ ግዶን አቄስ

. አቅም የሌለው ሰው ከሴትየዋ ሸርጥ ውስጥ ተኝቶ ያድራል

.. የፈራ የእናቱ ልጅ ነው

.. ፈሪ ለእናቱ

2223. ዎልቅ በይነ ኡር ዎታን ኩንዴስ

. አቅም የሌለው በሩጫ ላይ እያለ ይወድቃል

.. አቅሙን አያውቅ ቶሎ አይታረቅ

.. አለአቅሙ ጥሬ መቃሙ

2224. ዎልቅ በይነይ ገጠን ዱሬስ

. አቅም የሌለው ከዳር ይጨፍራል

.. ሰው እንደቤቱ እንጂ እንደ ጐረቤቱ አያድርም

.. አቅምን አውቆ መኖር ጥሩ ነው ታላቅ ችሎታ ነው

2225. ዎልቅ እጦይ ኦዶ ዩዴስ

. አቅሙ ሲያቅተው ወሬ ያስወራል

.. ዱላ እስከሚገኝ በክርንዎ ያዝግሙ

2226. ዎልቅ እጦይ ጦሰን ጨዬስ

. ማሸነፍ ያቃተው በአምላክ ይራገማል

.. ለአምላክ ልንገረው ለማያስቀረው

2227. ዎሊ ሆእን ዶሜ ጉፔስ

. ጭፈራ ሲደራ ቆማጣም ይገባበታል

.. አፍ ያለው ድዳ ያናግራል

2228. ዎመይ ዴእሽን ዎሰይ ኤኪስ

. የወቀሰ እያለ የለመነ ይወስዳል

.. አመሌ አወጣኝ ከማህበሬ

2229. ዎማ ከትን (ካሢና) ቁንጡዋ ዎሴስ

. ሽምታ ብትጋግር ቅራፊ (ቅርፊት) ይለምናል

. የለማኝ ለማኝ ቁርጮዬን ቀማኝ

2230. ዎረ ጊን ዎቴስ፣ ሼምቱዋ አሻ ግን ፖርቀዬስ

. ግደል ሲሉት ያኖራል፣ ነፍስ አድን ሲባል ያሰቃያል

.. አይዋጥ አይተፋ መላው የጠፋ

2231. ዎረነ ገይ ዎዘነ አይፍያ ዬርንከ አጌነ

. እገላለሁ ያለ ልቡን ቢስሙትም አይተውም

.. ሊወጋ የመጣ ጌታዬ ቢሉት አይመለስም

2232. ዎረናደን ይድ ሀይቀናደን ሃን ስሜስ

. እንደሚገ፤ ል መጥቶ እንደሚሞት ሆኖ ይመለሳል

.. እዩኝ እዩ፣ የለ ደብቁኝ ደብቁኝ ይላል

2233. ዎረይኔ ዬሎይኔ ዎንታረ አቴስ

. ግዳይና ልጅ መውለድ በጥዋት ይቀራል

.. ሁሉም በጊዜ ያምራል

.. ጊዜ ያለው ጊዜ አይጠብቅ

2234. ዎራ እምደ ጦሰው ቄፍየን ባልያ ኤሳ

. ግዳይ የምታስጥል ጌታ ክንፍ ላይ ላባ ትከል

.. እከክ የሰጠ ጌታ ጥፍር አይነሣም

.. ሞትን የሰጠ ጌታ ቀባሪ አይነሣም

2235. ዎር ቤእደ ፐረይ ዱሩማ ቤእድ ገርማሜስ

. ገድሎ ያየ ፈረስ ጉቶ አይቶ ይበረግጋል

.. የለመደች ጦጣ ሁልጊዜ ሽምጠጣ

2236. ዎር ኤርየ ፐረይ ዱሩማ ቤእድ በርጋጌስ

. ገድሎ የለመደ ፈረስ ጉቶ አይቶ ይደነብራል

.. የለመደች ጦጣ ሁልጊዜ ሽምጠጣ

2237. ዎር ኤርደ ፐረይ ዱሩማ ቤእ ደገሜስ

. ገድሎ የለመደ ፈረስ ጉቶ አይቶ ይደነብራል

.. የለመደች ጦጣ ሁልጊዜ ሽምጠጣ

2238. ዎር ኤሬሽን ሞግ ኤሬነ ቦለ ጦሳ፣ ሰእ ኤሬሽን ጮም ኤሬነ ስንተ አቻ

. ገድሎ የማይቀበር ጌታ እግዚአብሔር፣ ገምጦ የማያኝክ የፊት ጥርስ

.. ጀምሮ የማይፈጽም ፈጭ የማያልም

2239. ዎርየ ሀርግያፔ ደርኩዋ ከሎይ ኢ.ታ

. ከሚገድል በሽታ የጓሮ መራቆት የከፋ ነው

.. ከማይረባ ኑሮ ሞት ይሻላል

2240. ዎርየ ቶረራይ ዠንእድከ ቀንጤስ

. የሚገድል ጦር ተኝቶም ይቆርጣል

.. የሚያጠግብ ቂጣ ከምጣዱ የሚወጣ ጥጃ ከገመዱ

2241. ዎርየ ኡረይኔ ፔንጌን፣ ሀይቅየ ሼምፖይኔ ቆሬን

. የሚገለውም ሰው ከበር፣ የሚሞተው ሰው ነፍስም ከአንገት

.. በድንገት አህያ ከጅብ ቤት

.. ፊላጊና ተፈላጊ ሲገናኙ

2242. ዎርየው ዴንድን ቆነሼ ቃጨስ

. ውሸታም ሲነሣ የደረቀ ኮባ ይንኮሻኮሻል

.. ሀሰተኛ በቃሉ ስደተኛ በቅሉ ያስታውቃል

2243. ዎርደ አሩሲ ቆርገና፣ ሜደ አንኮይ ምታ ግእን ምሽሪያ ተነአ ኤሀ ኤሀ ዬገ ገውሱ

. የገደለው አሩሲ ቆርጋ ደርሶ፣ የበላው አሞራ ዛፍ ላይ ከወጣ በኋላ ልጄን አምጥተህ ጣልልኝ ትላላች እናት

.. አህያ በሞተች ባመቷ ኩርኩር

2244. ዎርደንቺይ ጐዴነን ዎጨስ

. ውሸታም ሳያሳድዱት ይሮጣል

.. ሌባ ሌባ ሲሉት ከሸንጎ ይሮጣል

2245. ዎርዱወን ዎዶሮይ በያናፔ ቱማገን በቁሎይ በዮ

. በውሸት ገመድ ከሚጠፋ በእውነት በቅሎ ይጥፋ

.. በውል ከሄደች በቅሎዬ ያለውል የሄደች ጭብጦዬ

2246. ዎርዱዋ ሾሮይ ናኡ ይምፑዋፔኔ፣ ናሉ ብራፔኔ እሱዋ ጠዬነ

. የሀሰተኛ ጐረቤት ከሁለት ጡጫ ወይም ከሁለት ብር አንዱን አያጣም

.. ላም እሣት ወለደች እንዳትልሰው ፈጃት እንዳትተወው ልጇ ሆነባት

2247. ዎርዱዋ ዳጐን ጌንእ ክዬስ

. በሀሰተኛ ደቦ ላይ ሚዳቋ ይወጣል

.. እባብ የልቡን አይቶ እግር ነሣው

2248. ዎርዶ መሮይ በደለይ ከጥን ዬስ

. ሀሰተኛ ጠንቋይ በቆሎ ሲበስል ይመጣል

.. ለወቀጣ አንድም ሰው አልመጣ፤ ለመጠጡ ከየጐሬው ወጡ
.. ለስራ ያልደረሱ ለመብል ያላነሱ

2249. ዎርዶ ኦደናፔ ዎስ ማነ ጌስ
. ውሸት ከመናገር ለምኜ እበላለሁ ይላል
.. እውነት ተናግሮ ከመሸበት ማደር

2250. ዎርዶ ዎንጠፌይ ጥሎ ካታ ኀይርሴስ
. ጥፋተኛ ሙርጥ ደህናውን ፍሬ ያስቆርጣል
.. ለህጥአን የመጣ ለፃድቃን ይተርፋል

2251. ዎርዶ ዮትን ዎንቶ የሼስ
. ሀሰት ቢናገሩ ነገ ያስፈራል
.. ለእብለት ስር የለው ለእባብ እግር የለው

2252. ዎርዶይ ሀይቅን ዱሮይ ቦኪድ አቅንካ አው ግዴነ
. ሀሰተኛ ሰው ሲሞት መቃብር ሲቆፍሩ ቢያድሩም አይበቃውም
.. የሰው ግብሩ አይለየው እስከ መቃብሩ

2253. ዎርዶይ ቱመን ላሜቴነ
. ሀሰት በእውነት አይለወጥም
.. የእውነት ዘንግ ትመነምናለች እንጂ አትሰበርም

2254. ዎርዶይ ዎሴትኮ ጥሎይ ሸትሜነ
. ውሸታም ቢወራረድ እውነተኛ ሰው አይረታውም
.. ሀሰቱ ስለበዛ እውነቱ ሆነ ዋዛ

2255. ዎርዶይ ገረን ዋስን ጥሎይ ኬታፔ ከይድ ሀይቄስ
. ሀሰተኛ ቆላ ሆኖ ቢጮህ እውነተኛ ከቤት ወጥቶ ይሞታል
.. ለህጥአን የመጣ ለፃድቃን ይተርፋል

2256. ዎርዶይ ጥለነው ጫቄስ፤ ሀይቀነ ኡረይ አተነ ኡራደን ዎጤስ
. ሀሰተኛ እውነተኛ ለመምሰል ይምላል፤ የሚሞት ሰው እንደሚድን ይሮጣል

.. ላይቀር ሙቱ መንጠራራቱ

.. ላታመልጪኝ አታሩጪኝ

2257. ዎርዶይ ጥለናዳን ጫቄስ

. ሀሰተኛ እውነተኛ ለመምሰል ይምላል

.. የሌባ አይነ ደረቅ መልሶ ልብ ያድርቅ

2258. ዎርዶይ ጥለናደን ጫቄስ፣ ከይሶይ ሚአናደን ዎጤስ

. ሀሰተኛ እስከሚታመን ይምላል፣ ሌባ እስከሚሰበር ይሮጣል

.. ሀሰተኛ በቃሉ ስደተኛ በቅሉ

.. ሀሰተኛ ብርቱ ወንጀለኛ

2259. ዎርዶይኔ ዋንጨይኔ ዶነን ኤኪስ

. ውሸታምና ዋንጫ ከአፍ ይወስዳል

.. ሀሰተኛ በቃሉ ስደተኛ በቅሉ

2260. ዎሪደይ ገይሮ ኤሬስ

. የገደለ መፎከር ያውቅበታል

.. ሀ ባሉ ተዝካር በሉ

.. ማን ይናገር የነበረ ማን ያርዳ የቀበረ

2261. ዎሬ ያጥን በዞን ሶቦይ ቃጤስ

. ወሬ ሲሮጥ ጫካ ውስጥ ያለው «ሶቦ» እንጨት ይንቀሳቀሳል

.. አንድ እግርኛን አስር ፈረሰኛ አይመልሰውም

2262. ዎሬረ ማጫስያ ዎጣ ላፑንቶ ቴቀውሱ

. ወሬኛ ሴት የድንጋይ ወፍጮ ሰባት ጊዜ ትደቅናለች

.. አፍ ያበዛ ጥበቡ ዋዛ

2263. ዎሬረይ ዎጥን ቆናሺ ቃጤስ

. ወሬኛ (ቀበጥባጣ) ሰው ሲሮጥ ደረቅ ኮባ ይነቃነቃል

.. ዋሽ ቢሉኝ እዋሻለሁ ንፋስ በወጥመድ እይዛለሁ

2264. ዎሬረይ ዎጥን ዎገ አኄ ዘኤስ

. ወሬኛ ሲሮጥ አውራ ጐዳና ይሰነጠቃል

.. ወሬኛ ሚስት ዘርዛራ ወንፊት

2265. ዎሬነ ሀርግየን ለግያኔ አለጋ ፓጩ·ቴስ

. በማይገድል በሽታ ባእድና ወዳጅን ይታዘቧል

.. ጥቂት ታመህ ወዳጅና ጠላትህን ለይ

2266. ዎሬነ ሽሬቾይ ዎረና ጊድ ሀይታ ሉኪስ

. የማይገድል ጠንቋይ እገላለሁ ብሎ ጀሮውን ይበሳል

.. ገና ለገና ይመታል በገና

.. ላም አለኝ በሰማይ ወተቷንም አላይ

2267. ዎሬነ ኡረይ ዎገ ቶራ አይቁስ

. የማይገድል ሰው ትልቅ ጦር ይይዛል

.. የፈሪ ዱላ አስር ነው

2268. ዎሬነይ ናኡ ቶራ አይቁስ

. የማይገድል ሁለት ጦር ይይዛል

.. የፈሪ ዱላ አስር ነው

2269. ዎሰ ማታ ዎንጠፈይ ጉሴስ

. ተለምኖ የመጣን ወተት ብልት ያፈሰዋል

.. እነሰ ሲሉት ተቀነሰ

2270. ዎሰራስ ዎሬረ፣ ሾሮስ ሾሎተ

. ለጠላት ጠንክር፣ ለጐረቤት አጐንብስ

.. ለወዳጅ የማር ወለላ ለጠላት እሾህ አሜከላ

2271. ዎሰይኔ ጠለሄኔ እማ ኤኪስ

. ለማኝና ውቃቢ የሰጡትን ይወስዳል

.. የተቸገረ እርጉዝ ያገባል

2272. ምስልየው ጌለይደ ጠንታ ጌንቶፐ

. ለዘፈን ስትገቢ ጡትሽን አትሸፍኝ

.. ከለገሱ አይቀር ይንጋለሉ

.. ቀድሞም ባልዘፈንሽ ከዘፈንሽም ባላፈርሽ

2273. ምሲ ኤሂድ ባዋ አያነው አጬስ

. ለምኖ አምጥቶ ለአባቱ ውቃቢ ስለት ያደርሳል

.. አንቃ ለራሱ አይበቃ ለሰው ጠበቃ

.. ለራሱ አያውቅ ነዳይ ቅቤ ለመነ ላዋይ

2274. ምሲ ኤከይ አሰው ግቬስ

. ለምኖ ያገኘ ለሰው ያድላል

.. አንቃ ለራሱ አይበቃ ለሰው ጠበቃ

2275. ምሲ ኤከይ ጬልዲ ምሬስ

. ለምኖ ያገባ አንቆ ይገድላል

.. ሲያልቅ አያምር

2276. ምሲን እጥደ ምሽርያ ምስ ደቦተውሱ

. ቢለምኗት እምቢ ያለች ሴት ለምና ትታረቃለች

.. ሲስሟት ትታ ሲስቧት

2277. ምሲን እጥዳረ ጎቼን በውሱ

. ተለምና እምቢ ያለች ቢጐትቷት ትሄዳለች

.. ሲስሟት ትታ ሲስቧት

2278. ምሲን ኢጥድ ምሲ ሜስ

. ቢለምኑት እምቢ ብሎ ለምኖ ይበላል

.. ሲስሟት ትታ ሲስቧት

2279. ምሲን ጌልዳጌ ቁፍያረ ክይድ ቤስ

. ተለምኖ የገባ ሲያስሉት ወልቆ ይሄዳል

.. ላይጠቅሙኝ ቂጤን አረጠበኝ

2280. ዎሲድ ኤሂዶ መይዴ ሽምድ ኤሂዶ ዎጣ ላቴስ

. ለምነው ያመጡት መጅ ተገዝቶ የመጣውን ወፍጮ ይወርሣል

.. ፊት ከወጣ ጆሮ ኋላ የበቀለ ቀንድ ይበልጣል

2281. ዎሲድ ኤፊዴ ጮ ኤፊዴ

. ለምኖ ወሰደ ወይስ ዝም ብሎ ወሰደ

.. እንዲያው ለነገሩ አለሸወይ ባገሩ

2282. ዎሲዶ ዳነይ ቀቼስ

. የለመኑት ዳኛ ያስራል

.. አወቅሁሽ ናቅሁሽ

2283. ዎሴነን ጌልደ ዎንጠፈይ ቁፍን ክዩነን እጬስ

. ሳይለምኑት የገባ ብልት ቢስሉ አልወጣም ይላል

.. ያልበሉት ዕዳ ያልጠሩት እንግዳ

2284. ዎብያ ቦለን ዎራጃይ ጉጄቱስ

. በአንካሳ ላይ ጦርነት ይመጣበታል

.. በቦሃ ላይ ቆረቆር

2285. ዎቤ በ ቤታ በው ኤረስ

. አንካሳ የራሱን አካሄድ ራሱ ያውቃል

.. የሚበጀውን ባለቤቱ ያውቃል

2286. ዎተ ኣተ ጊሽን ዎዴ ኣዴስ

. ውረድ ቀና በል ሲባል ጊዜ ያልፋል

.. ጊዜ ወርቅ ነው ግን ኃላፊ ነው

2287. ዎታ ደሮይ ባሰን ኬሴስ

. ብዙ መንቀኛቀኛ ጠላት ካለበት ያደርሳል

.. አለማረፍ ጣር ያበዛል

2288. ዎታ ደሮይ ጦኔነ፣ ዎልቃ ደሮይ ጦኔስ

. የሩጫ ብዛት ሣይሆን የሚያሸንፈው ጉልበተኛ ነው

.. ዱባና ቅል አበቃቀሉ ለየቅል

2289. ዎታ ጉጪያ ከና ጐደሬ ሞ

. ለሩጫ የሚያንስ ውሻ ጅብ ይብላው

.. ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ

2290. ዎታፔ ጎንዶርስ ኣሮ፣ ኣሾፔ ሜቄት መልኦ

. ከሩጫ መንከባለል ይሻላል፣ ከስጋ አጥንት ይጣፍጣል

.. ምርት ከገለባ ግዳይ ከሰለባ

2291. ዎነ ዎዘናሜነን ለሆ ዎዘነሜስ

. ፊት ልባም ያልሆነው ለመዋሸት ልባም ይሆናል

.. ቀድሞ ነበር እንጂ መጥኖ መደቆስ፣ አሁን ምን ያደርጋል ድስት ጥዶ ማልቀስ

2292. ዎነጐ ዎንሰን ዎደ ኤቀ ናገ ገውሱ ጌለእያ

. የቅድሙ ሰውዬ ከዚያ ቦታ ወርደህ ጠብቀኝ ትላለች ልጃገረድዋ

.. የለመደች ጦጣ ሁልጊዜ ሽምጠጣ

2293. ዎን ቢታ ምየ ነእዮ ዳዋኔ ሹቸን ጨዴስ

. ቀድሞውን አፈር የምትበላዋን ልጅ ዳዋና (ስም) በድንጋይ ይመታል

.. እንኳን ዘንቦብሽ እንዲያውም ጤዛ ነሽ

2294. ዎን ናገ ሚነሆ አይስ ናጌነን ማዲ?

. ጠብቀህ አትበላም ነበር ለምን ሣትጠብቅ በላህ?

.. የቸኮለች አፍሣ ለቀመች

2295. ዎን ኢተ ሲሬ ዱጣ

. ቀድሞም መጥፎ አፍንጫ ቆራጣ

.. እንኳን ዘንቦብሽ እንዲያውም ጤዛ ነሽ

2296. ዎን ዋኖ ግየ ዱሊያ ዎሌ ቀንጤስ

. ፊትም ምን ልሁን የሚለውን ቂጥ የአገዳ ልጣጭ ይቆርጠዋል

.. እንኳን ዘንቦብሽ እንዲያውም ጤዛ ነሽ

2297. ዎን ዎግያሬ ዋነ ፖገንዲ?

. ድሮ የምትንቀባረሪ አሁንስ እንዴት ትሆኚ?

.. እንኳን ዘንቦብሽ ወትሮም ጤዛ ነሽ

2298. ዎንተ አው ክለሆትድ እጤስ፣ አመርስ ይድ ዎስ ሜስ

. ጥዋት አባት ጠግቦ እንቢ ይላል፣ ማታ ተመልሶ ለምኖ ይበላል

.. ሲስሚት ትታ ሲስቧል

2299. ዎንተናኮ ዎኒ ዎንተነ፣ ተ ኡኬተ ተው እመ ማነ

. የሚነጋ ቢሆን ኖሮ እስካሁን ይነጋ ነበር ጭብጦዬን ስጡኝና ልብላ

.. ጊዜ የሌለው የለም ግን ከእድሉ የሚያልፍ የለም

2300. ዎንተይ ዎዘና እሜስ

. ነቀፌታ ልባም ያደርጋል

.. ብልህ ከስህተቱ ይማራል

2301. ዎንታረ ሜንታ ዎሪየ ጋሞይ አመርስ አቅርስ መጤስ

. በወጣትነት ጊዜ ጕሽ የሚገድል አንበሳ ሲያረጅ እንቁራሪት ይለቅማል

.. ካረጁ አይበጁ

.. ሲያልቅ አያምር

2302. ዎንቲ ዎንተናጋኔ ዎርቅ ዮተናጋኔ ኦን ኤሪ

. ነገ ምን እንደሚነጋና፣ ንጉስ ምን እንደሚናገር ማን ያውቃል

.. የነገን ነገር ማን ያውቃል

2303. ዎንቴነን ዋሲደ ጐደሬ ተ ኣዋ አይሲ

. ሣይነጋ የጮኸ ጅብ አባቴን ያሣድራልን

.. ይህቺ ባቄላ ካደረች አትቆረጠምም

.. ወይ ጣጣ ምን ነገር መጣ

2304. ዎንቴነን ዋሲደ ጕደሬ ተ አይዮ አሺ?

. ሣይነጋ የሙኸ ጅብ እናቴን ያስቀራታል ወይ

.. ይህቺ ባቄላ ካደረች አትቆረጠምም

.. ወይ ጣጣ ምን ነገር መጣ

2305. ዎንቶ ዎንተነ፣ ዎርቀይ ዮተነ

. ነገ ይነጋል ወርቅ (ንጉስ) ይናገራል

.. እውነትና ንጋት እያደር ይጠራል

2306. ዎንቶ ጊደበይ ዎዴ ገቴስ

. ነገ ያሉት ነገር አመት ይቆያል

.. ጊዜ ያለው ጊዜን አይጠብቅም

.. ነገ ለራሱ ይነጋል

2307. ዎንቶስ ዎንቶፖ ዎዲነው ጊጐፖ

. ለነገ አይንጋ አሸከር አይሳካለት

.. ከእጇ በጉንጩ

2308. ዎንደፊሪያ ደሮይ ደፊን ዱጤነ፣ ቃልቻ ጐሜ ኬሲን ውሬነ

. የደጋን ጅማት ሲስቡት አይበጠስም፣ የቃልቻ እርግማን ቢፈታ አይለቅም

.. ቀድሞ ሰኞን አለመሆን

2309. ዎንጌሬሎይ ዴሻ መለትድ ዴሸ ሜስ

. ተኩላ ፍየል መስሎ ፍየል ይበላል

.. የቀበሮ ባህታዊ ከበጐች መሀል ይፀልያል

2310. ዎንጠፋ ኮይያረ ካታ ሻቴተውሱ

. ብልት የምትፈልግ ሴት ፍሬውን ትጠየፋለች

.. ከስጋው አውጡልኝ ከመረቁ ያመኛ ነኝ

2311. ዎንጠፍ ኦቲዶ ሜቱወን ቡንኪ ጎይሬቴስ

. ብልት በሰራው ስህተት ፍሬ ይቆረጣል

.. አይጥ በበላ ዳዋ ተመታ

2312. ዎካሌይ በይናኮ አማር ዱዴ

. ቱርጅማን ባይኖር ኖሮ አማራ ከዱዳ ይቆጠር ነበር

.. ማወቅ መላቅ አለማወቅ መናቅ

2313. ዎዘነይ በይነ ሀርጌ ከሎ ዝንእስ ሰኬስ

. ልብ የሚነሣ በሽታ ራቁት ያስተኛል

.. ልብ የሌላት ውሻ ማር ትቀላውጣለች

2314. ዎዘነይ አዝና፣ ዎዘንትያይ አ ቦይነ

. ልብ ባል ነው፣ ልባም የሚያደርግ የሱ ጎዳሬ ነው

.. ላም የዋለችበትን ትመስላለች

2315. ዎዘነይ ከረናፔ አሰይ ከሮ

. ልብህ ከሚንቅህ ሰው ቢንቅህ ይሻላል

.. አፍ ሲዋሽ ሆድ ይታዘባል

2316. ዎዘነይ ዋይን ሰልኬተይ ሰዌስ

. ልብ ሲከዳ ፍርፋሪ ይሸታል

.. ሰነፍ አይፀድቅም

2317. ዎዘነይ ዎሪን አዝነይ ዩዴስ

. ልብ ሲጠፋ ባል ይፈታል

.. ማወቅ መላቅ አለማወቅ መናቅ

2318. ዎዘነይ ዎርዶሮ አዝነይ ወዴስ

. ልብ የገደላትን ባል ይደበድባታል

.. ሰነፍ ሴት እድል የላትም ለንብረት

2319. ዎዘና ዎቤ አዝና ዎብያረ ገቴስ

. የልብ ሰንካላ ከአንካሳ ባል ጋር ያገናኛል

.. እባብ የልቡን አይቶ እግር ነሣው

2320. ምዘና ምቤ ኦግየን አቅን፣ ጌዲያ ምቤ ሶ ገከድ አቴስ

. የልብ አንካሳ እመንገድ ሲያድር፣ የእግር አንካሳ እቤቱ ደርሶ ያድራል

.. መርፌ ሲለግም ቅቤ አይወጋም

2321. ምዘና ፐጨይ አወ ጊድ አግነን ድባብያ ኦይቴስ

. ሞኝ (ልበቢስ) ፀሐይ መስሎት በጨረቃ ዣንጥላ ይዘረጋል

.. ሞኝ እንደመከሩት

.. ሲወልዱ አይታ በጠጧን ጣለች

2322. ምዘና ፐጫ ምሽርያ ደረን ዴእየ ኦለሙዋ ማደ ሶን ኡተደ

አወ ዞኩወ ቤሰውሱ ከሬን ኡተደ ኡሉዋ ሶ ተመ ቤሰይሱ

. ልበቢስ ሴት ከጓሮ ስራስር በልታ እቤት ተቀምጣ ውጪ ላለው ፀሐይ ጀርባዋን ታሳያለች፣ ውጪ ተቀምጣ ሆዷን እቤት ላለው እሳት ታሳያለች

. መርፌ መግቢያዋን እንጂ መውጫዋን አታውቅም

. ሞኝ እንደመከሩት

2323. ምዘናረ ጊጌነይ ምዘነ ሀርጌ

. ከልብ ጋር የማይስማማ የልብ በሽታ ነው

.. የልብ ሣይደርስ እድሜ ይደርስ

2324. ምዘን በይነ ሃተይ ዞአ፣ አቦይ ዳቦይ በይነ ገዴ ጋዞ

. ልብ የሌለው ወንዝ ‹ዞአ› ነው፣ አጐት ዘመድ የሌለበት አገር «ጋዞ» ነው

.. ከዘመድ የራቀ ሰውና እበረሀ ቀኑ የጨለመበት አውሬ አንድ ናቸው

2325. ምዘን በይነ ቆሬ ኡስታ ሲት ሜነ

. ልብ የሌለው ጉረሮ መበያውን ቆጥቦ አይበላም

.. ሞኝ የእለቱን ብልጥ ያመቱን

2326. ዎዘን በይነ ወንገኔ አዝን በይነ ደንገኔ ናአይ አግየን ገይቶሶነ

. ልብ የሌላት ወንጌና ባል የሌላት ደንጌ ሁለቱ መንገድ ላይ ይገናኛሉ

.. ግም ለግም አብረህ አዝግም

2327. ዎዘን በይነ ዎንድራደ ሀል ገራ ኪቴስ

. ልብ የሌለውን ወንድራድን ወደ ሀሊ ቆላ ይልኩታል

.. ሞኝ ባያፍር የሞኝ ዘመድ ያፍር

.. ሞኝ እንደመከሩት

2328. ዎዘን በይነ ዎንድራዴኔ አይፌ በይነ ማንዳፌሮይኔ ፐርዲን ኤክኬ ሸወ በ ሻሪሰነ ጌስ

. ልብ የሌለው ወንድይራድና አይን የሌለው ማንደፍሮት በፈረዱት አልረታም ሸዋ ሄጄ አስሽራለሁ ይላል

.. ለበላይም የበላይ አለ

2329. ዎዘንትያይ አዝነ

. ልባም የሚያደርገው ባል ነው

.. የባል ደግነቱ ባትናገር ሚስቱ

2330. ዎይ ነምሰ ጉተ ግደከ፣ ዎይ ምድግን ያከ

. ወይ ትንሽ የምትበላ አይደለህ፣ ወይ ከበላን በኋላ አልመጣህ

.. ለሆዳም በሬ ጭድ ያዝለታል

2331. ዎይሻ ቶክድ ቦለድያ ዬጤስ

. ቀርከሃ ተሸክሞ ሎጋው ሽቦ ይዘፍናል

.. ሞኝ ባያፍር የሞኝ ዘመድ ያፍር

2332. ዎይሸይ ዎንተ ማይድ አመርስ ካሎቴስ

. ቀርከሃ ጥዋት ለብሶ ማታ ይራቆታል

.. ሲያልቅ አያምር

2333. ዎደለው ዬሎ ነአ ጋሌኔ በቁስ

. ለፍላጐቷ ብላ የወለደችውን ልጅ ጋኔን ይመታዋል

.. ሣይጠሩት የመጣ ሣይጠግብ ይሄዳል

2334. ዎድራ በቅን መጨቴተይ የዬስ

. ጭን ሲመታ ብልት ይፈራል

.. ነግ በኔ

2335. ዎድያ ዎደሰይ ጤስኔ ኮዬነ ጤለነውኔ አዬነ

. የዘመኑ ጉረምሳ ለጥሪም ወይ አይልም፣ ለማየትም አያኮራም (አይን አይሞላም)

.. ሰው መሣይ በሽንጉ

.. ሲያዩት ያላማረ ሲበሉት ያቅራል

2336. ዎዴ እሜዶ ቡሌ ሹቻ ሜንቴስ

. ጊዜ የሰጠው አንኮላ ድንጋይ ይሰብራል

.. ጊዜ የሰጠው ቅል ድንጋይ ይሰብራል

2337. ዎዴ እሞ በጨይ ሹቻ ሜንቴስ

. ጊዜ የሰጠው ቅል ድንጋይ ይሰብራል

.. ጊዜ የሰጠው ቅል ድንጋይ ይሰብራል

2338. ዎዴ ኬሀነ ግን ኦምቦሸ አዝና ጌሊኬ ገውሱ

. ጊዜው ይበጃል ሲባል ኦምቦሼ ባል አላገባም አለች

.. የሚበጀውን ባለቤቱ ያውቃል

.. ከበለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው

.. ከማያውቁት መልአክ የሚያውቁት ሰይጣን

2339. ዎዴ ውሪን ዎሩዋን ዜርን ትየይ ገኬነ

. ጊዜ ሲያልፍ በአዛባ ላይ የተዘራውም አይደርስም

.. ጊዜ ወርቅ ነው ግን ኃላፊ ነው

2340. ዎዴ ዎርዶቲን ቃልቾይ ሰንተ ሜስ

. ጊዜ ሲዋሽ ቃልቻ የወር ጉመን ይበላል

.. ጊዜ ሲከዳ መሬት ያድጣል

2341. ዎዴ ዎርዶትን ኩቶይ ኪታ ሆክ ጌሌስ

. ጊዜ ሲከዳ ዶሮ አጕንብሶ እቤት ይገባል

.. እስላም ካበለ ቀን ዘነበለ

2342. ዎዴ ዎርዶትን ገረን ጋሼ ኩቱኩልኤስ

. ጊዜ ሲዋሽ ቆላ ጤፍ ይጋሽባል

.. ጊዜ ሲከዳ መሬት ያድጣል

2343. ዎዴ ዎርዶትን ገረውያ ዋሞተውሱ

. ጊዜው ሲዋሽ ድመት ታመነኻካለች

.. የተገላቢጦሽ አህያ ወደሊጥ ውሻ ወደ ግጦሽ

2344. ዎዴ ዎቂን ሀሬ ሼኤስ

. ሁኔታ ሲመቻች አህያ ይሸናል

.. ሲዳላ ነው እዩዬ

2345. ዎዴ ዎጥ ውሬስ

. ጊዜው ሮጦ አለቀ

.. ጊዜ ወርቅ ነው ግን ኃላፊ ነው

2346. ዎዶሩዋ ምያረ ቢን ብጣላ ምያረ የውሱ

. ገመድ የምትበላዋ ስትሄድ ልጓም የምትበላ ትመጣለች

.. የባሰ አለና ሚስትህን አትፍታ

2347. ዎዶሩዋ ምያሮ ኢተ ግን ብረታ ምያረ የውሱ

. ገመድ የምትበላዋ መጥፎ ስትበላ ብረት የምትቆረጥም ትመጣለች

.. የባሰ አለና ሚስትህን አትፍታ

2348. ዎዶሩዋ ምያሮ ኢተ ጊ በይዝን ሎሁዋ ምያረ የውሱ

. ገመድ የምትበላዋን መጥፎ ናት ብሎ ቢሸጥ ለኮ የምትበላ ትመጣለች

.. የባሰ አለና ሚስትህን አትፍታ

2349. ዎገ ምተይ ውልን ቤጤ ደሬስ

. ትልቅ ዛፍ ሲወድቅ ጠገራ ይበዛበታል

.. በወደቀ ዛፍ ላይ ምሣር ይበዛበታል

2350. ዎገ ሜቶይ አይቤ ግን ኮሽ ጌቴስ

. ትልቅ ችግር ምንድነው ቢባል ረሃብ ነው ይላሉ

.. የሆድ ነገር ሆድ ይቆርጣል

2351. ዎገ ሰሮተይ ዝላሳ ኤሄስ

. ትልቅ ሰላምታ እዮዮን ያስከትላል

.. አጥብቆ ጠያቂ የእናቱን ሞት ይረዳል

2352. ዎገ አሰይ ዴሻ ማታ ኡይዮጌ ጠሌተናሰ ጌቴስ፣ ቂሪ አስ ኡይዮጌ ቀጠናስ ጌቴስ

. ትልቅ ሰው የፍየል ወተት የሚጠጣው ለመድሀኒትነት ነው ይባላል፣ ድሃ ሲጠጣ ችጋር ይዞት ነው ይሉታል

.. ላለው ቅንጭብ ያረግዳል

2353. ዎገ ኡተን ጎብ ባወ

. ትልቅ እንሰት ቅርፊት (ጐባ) የለውም

.. ትልቅ ቤት ትልቅ ችግር አለ

.. ቢከፍቱት ተልባ

2354. ዎገ ኦግያረ ጐደሬ አሰይ ቤስ ጊሽን፣ አሰይ ጎደሬ ቤስ ጊሽን፣ ሜለ አቂስ

. አውራ መንገድ ጅቡ ሰው ይሄድበታል ሲል፣ ሰው ደግሞ ጅብ ይሄድበታል ሲል በመሃል ጦሙን ያድራል

.. እባብ ለእባብ ይተያያል ካብ ለካብ

2355. ዎገቴተይ ሽሞ ድጌነሽን ሽም ሺሽን በኦ ድጌስ

. ትልቅነት ከሽመታ አያድንም ግን የተሸመተውን ለመሸከም ያሳፍራል

.. የማያዘልቅ ፀሎት ለቅስፈት

.. ይሉኝታ የራስ አሊን ቤት የፈታ

2356. ዎገይ ዎረነ ጠይኮኔ የሼስ

. ትልቅ ባይገድልም ያስፈራል

. ረዥም ጦር ባይወጉበትም ያስፈራሩበታል

2357. ዎገይ ዎርዶቴስ ጩግየ ሰዎተውሱ

. ትልቅ ይዋሻል፣ አሮጊት ትገለሙታለች

.. ካረጁ አይበጁ

.. ሲያልቅ አያምር

2358. ዎጋጬ ቃቸይ እጥን ዙቃኑወን ቃጬስ

. ቀጥቃጭ መፋቅ ሲያቅተው በጉባ ይፍቃል

.. ሰነፍ ይፀድቃል ወይ ቢል በሬ ይወልዳል ወይ አለ ይባላል

2359. ዎግ በይነ ቢተን በል በይነ ምተይ ሞኬስ

. ስርዓት በሌበት አገር ባላ የሌለው እንጨት ይበቅላል

.. ስነስርዓት የሌለበት አገር ችግር አለ

.. አባት የሌለው ቤት ዳኛ የሌለበት ችሎት

2360. ዎግ ገይ ዎሰነ ከንቴስ

. እሺ ያለ ከጠላት እጅ ያመልጣል

.. መልካም ምላስ ቁጣን ታበርዳለች

.. እሺ ይበልጣል ከሺ

2361. ዎጠይደ ዩዳረ ጋብያ ኤክን ካጨደ ኪስዳረ ጋረ ጫላ ኤከውሱ

. ስትሮጥ የመጣችው ጋቢ ስታገኝ አርሳ ያወጣችው ድኩላ ቆዳ ትወስዳለች

.. ይታደጏል እንጂ አይታገሉም

.. አትሩጥ አንጋጥ

2362. ዎጥሽን ግጥዶጌ ዎጥሽን ብርሼቴስ

. ሲሮጡ የታጠቁት ሲሮጡ ይፈታል

.. ሲሮጡ የታጠቁት ሲሮጡ ይፈታል

2363. ዎጥን ዎጥን እጥን ጌንኤ አሾይ መልኤነ ጌስ

. ሩጦ ሲያቅተው ሚዳቋ ስጋሽ አይጣፍጥም ይላል

.. ያጣ ወሬ ነው

2364. ዎጥን ዎጥን ጌንእያ እጥን መልአነ ኔ አሾይ ጌስ

. ሮጦ ሮጦ ሚዳቋ ብታመልጠው ስጋሽ አይጣፍጥም ይላል

.. ያጣ ብዙ ያወራል

.. ሚዳቋ አባሮ ሲያቅተው ስጋሽም አይጣፍጥ አለ

2365. ዎጥየ ኡራ ጎድያበይ ጠይ ኤሬነ

. የሚሮጥን ሰው የሚያባርር አይጠፋም

.. በደንባራ በቅሎ ቃጭል ተጨምሮ

2366. ዎጥየ ጌኔሲያ ዝንእዳሮ ዴንተውሱ

. የምትሮጥ ሚዳቋ የተኛችውን ትቀሰቅሳለች

.. የሰው ሚስት ሚስቴን ገደለች

2367. ዎጥየ ፕራን ጠምአ ጉጄስ

. በሚጋልብ ፈረስ ብትር ይጨምራል

.. በደንባራ በቅሎ ቃጭል ተጨምሮ

.. ሆድ ለባሰው ማጭድ አታውሰው

2368. ዎጥየይ ዎንጀለ፣ ኤቅየይ ኡረ (ጉአቻ)

. ከሮጡ ወንጀለኛ፣ ከቆሙ አሽከር

.. ቢናገሩ አፈኛ ዝም ቢሉ ሞኝ
ከነገሩ ሁሉ ይሻ ጨነቀኝ

2369. ዎጥዳጋ ሚዳጌ ገኪስ

. የሮጠውን የበላ ይደርስበታል

.. የበላ በለጠ የሮጠ አመለጠ

## ዘ

2370. ዘልአንቸይ ላፑን ለይታ ገትድ ከሬ ገክድ ዎጤስ

. ነጋዴ ሰባት አመት ቆይቶ ከደጅ ሲደርስ ይሮጣል

.. ሰባት አመት የታወረ እውር ነገ አይንህ ይበራልሃል ቢሉት ዛሬ እንደምን አድሬ አለ

2371. ዘልእየን ዩይየ በቁልያ አቻ ፖቀ ቤሰውሱ

. ለሽያጭ የምትዞር በቅሎ ጥርሷን ፈልቅቃ ታሳያለች

.. የለመደች ጦጣ ሁልጊዜ ሽምጠጣ

2372. ዘልእየን ዩይየ ኡስያ አቻ ፖቀ ቤሰውሰ

. ለሽያጭ የምትዞር ጊደር ጥርሷን አግጥጣ ታሳያለች፣

..ላም የዋለችበትን ትመስላለች

.. የለመደች ጦጣ ሁል ጊዜ ሽምጠጣ

2373. ዘልእያ ኤርየ ኡስያ አቻ ፓቀ ቤሰውሱ

. ለሽያጭ የምትዞር ጊደር ጥርሷን ፈልቅቃ ታሳያለች

.. የለመደች ጦጣ ሁልጊዜ ሽምጠጣ

2374. ዘልኤ ቆሂዶ ፕላፔ ሾሮይ ፖረ ጌስ

. ንግድ ከጐዳው ይልቅ ጐረቤት ወየው ማለቱ ይከፋል

.. በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ

2375. ዘልኤ አይቤ ጋዩ፣ ዎሬ አይቤ ቁፌ

. ንግድ ምንድነው ትምባሆ፣ ትርፉ ምንድነው ሳል

.. አተርፍ ባይ አጉዳይ

2376. ዘማና ለይት ዘሬ ባጭራ ከቴስ

. በቀውጢ ዘመን እንሽላሊት (የቡላ ፍርፍር) «ባጭራ» ባህላዊ ምግብ ይሠራል

.. ዘመነ ግርምቢጥ ውሻ ወደ ግጦሽ አህያ ወደሊጥ

2377. ዘማና ጌለእያ ጠልታመደ ላሽሟ ዩጠውሱ

. የጠገበች ልጃገረድ የሰርግ ዘፈን ትዘፍናለች

.. ከይሉኝ አይል ጋር አይብ አትብላ

2378. ዘርቀቀ ዛሲ ኬንቼቸ ቦሉወን ገቴስ

. የመግደርደር ብዛት ከሀብታም አማች ጋር ያገናኛል

.. የረጋ ወተት ቅቤ ይወጣዋል

2379. ዘርያ ላፈይ መተን መተን ጬቂስ

. ትንሽ ዘር ወዲያው ወዲያው ይሮክርበታል

.. ትንሽ ያላት እንቅልፍ የላት

2380. ዘሬ ስገ ጊሽን ሰምፓ ቡሉዋ ውርሲስ

. እንሽላሊት ለማዳ ነው ሲባል የእርቦ ሙሉ ብቅል ይጨርሳል

.. ጅብ የኔ ነው ስለው ወናፊን ቀማኝ

2381. ዘጉዋ ውርሴነ ምሽርያ ካሜ ዙሜስ ገውሱ

. ደጃፍ መውጣት የማትችል ሴት መኪና ይድሃል ትላለች

.. ለተቀማጭ ሰማይ ቅርቡ ነው

.. ለአፍ ዳገት የለውም

2382. ዛላን ሼአፐ መይኔ መችዮ ኤኮፐ

. አለት ድንጋይ ላይ አትሽና መሀን ሚስት አታግባ፣

.. አባት ያበጀው ለልጅ ይበጀው

.. አስቦ መስራት ኋላ ከመፀፀት

2383. ዛላፔ ዛሰይ ይን ሃልጰናይ ሾቻ ግሼስ

. ከዛላ (አገር) ደላላ ሲመጣ ሀልጰና (ሰው) የእዝን ያድላል

.. ያልጠሩት ሰርገኛ በትረኛ

.. አያገባው ገብቶ አያወዛው ተቀብቶ

2384. ዛኩአይ ነአ ሳሱዋረ ዬሬቴስ

. የመሸታ ነጋዴን ልጅ ከነለሀጩ ይስሙታል

.. ሊበሉ የፈለጉትን አሞራ ስሙን ይሉታል ጅግራ

2385. ዛኪ ዛኩዋ አግን ኡዱንጤ አሀየን ኡዬስ

. ዛኪ መሸታ ብትጠምቅ ዝንብ በዱቤ ይጠጣል

.. ቂጠኛም ከውርዴ ይውላል

2386. ዛግያ ሀይተይ ፓሊ ፓሊድ ዛግያ ጠዱወን ዖዴስ

. የብርብራ ቅጠል በርሮ በርሮ ከብርብራ ስር ላይ ይወድቃል

.. ዘመድ ከዘመዱ አሀያ ካመዱ

2387. ዙንገ ዞልያ መውሽን ብየ ናተ ላፑና ዲቾናው ኤሀውሱ

. ዙንጌ ለራሷ አንድ ወቄት ትበላለች ግን የልጇን ሰባት ልጆች ለማሳደግ ታመጣለች

.. አባይ ማረፊያ የለው ግንድ ይዞ ይዞራል

2388. ዝቃታ ቀዜርሽን ባደ መጥሽን የውሱ

. ዝቃቴ ሲዘሩ ሄዳ ሲሰበስቡ ትመጣለች

.. ሰነፍ ገበሬ በመስከረም ያርማል

.. ቱሪናፋ ከስራ የለህ ከገበታ አትጠፋ

2389. ዝንቀ ዝንቀ ግየ ዋሼ አማሚ ኡተይ ዴእሽን ጎባ ዳኬ ኡታ ታ ማኔ ገውሱ ቁጠርስያ

. ግመጥ ግመጥ የሚለውን የአማሜ ዋሼን እንሰት ትቼ የዳኬ የደረቀ ኮባ እበላለሁ ወይ አለች አሉ ጃርት

.. መራጭ ይወድቃል ከምራጭ

.. ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ

2390. ዝንአ አቅዳረ ዝሜት መውሱ ጎየ አቅዳረ ጎፍኔ መውሱ

. ተኝታ ያደረች ሻኛ ስትበላ ለፍታ ያደረች ሳምባ ትባላለች

.. አትፋጥ አንጋጥ

2391. ዝንአዳ ይያረ ዝንአነው ቢያሮ ከንያ ገውሱ

. ተኝታ የምትመጣ ለመተኛት የምትሄደዋን ውሻ ትላለች

.. ሞኝ አያውቁብኝ ባይ

2392. ዝንእዳጋ ዴንተ ጊዶጌ በው ዝንኤስ

. የተኛውን ቀስቅስ የተባለው ለራሱ ይተኛል

.. የሰው መላክተኛ የልብ አያደርስም

.. የቁራ መላክተኛ

2393. ዝንእድ ገይተነው ኤቅድ ሱጌቴስ

. ተኝቶ ለመገናኘት ቆሞ ይጋፋል

.. የዘፈን ዳርዳሩ እስክስታ ነው

2394. ዝንኦ ኤራሳሽን ጢኮ ኤሬናነ

. ማስረገዝ እንጂ ማረስ የማታውቅ

.. እንካን የማያውቅ አምጣን ማን አስተማረው

2395. ዝንዞይኔ ኡዱንጤኔ ማበራ ኡዮሶነ

. ጢንዚዛና ዝንብ ማህበር ይጠጣሉ

.. ግም ለግም አብረህ አዝግም

2396. ዝኔ ማለዶ ዎዘና ሀች ማለዶ ዎዘነይ ከሬስ ጌቴስ

. የትናንትን ጥዋት ልብ የዛሬ ጥዋት ልብ ይንቃል ይባላል

.. ልብ የሚገኘው በስልሳ ገንዘብ የሚገኘው በሰላሳ

2397. ዝገይ ፓሊ ፓሊድ በር ጠጶን ዎዴስ

. የዝግባ ቅጠል በርሮ በርሮ ከዝግባ ስር ይወድቃል

.. ዘመድ ከዘመዱ አህያ ካመዱ

2398. ዝግርሰይኔ ዎድሬይኔ ጉዩረ ዴኤስ

. ሀሜትና ባት ከወደኋላ ነው

.. ለወሬ የለው ፍሬ

.. ባልፈሱበት ቂጥ አያፍሩበት

2399. ዝግርሳዩ ነእያ በእን ዋሞተውሱ

. የሃሜተኛ ሴት ልጅ ታገዛላ ታመነኘካለች

.. የዘሬን ብተው ያንዘርዝረኝ

2400. ዚታው ባደ ዚዝያ ሜአስ ጌስ ኩቶይ

. ለመሰረር ሄጄ አንገቴን ተሰበርኩ ይላል አውራ ዶሮ

.. አተርፍ ባይ አጉዳይ

2401. ዜቀውሱ ግን ክሀየን ኡሌተውሱ

. ትገሚያለሽ ቢሏት ኩበት ትታጠናለች

.. ከድጡ ወደማጡ

.. ትሻልን ትቼ ትብስን አገባሁ

2402. ዞልዶ ኦይሰን ዞኩዋ ሶኪስ፣ ግዶ ዘኩዋ ተማ ቤሴስ

. በሞላላ እስር ቅቤ ጀርባውን ያሻል፣ መሀል ጀርባውን በእሣት ያሞቃል

.. ገንፎ ለጉንፋን ጥሩ ነው፣ እግረ መንገዱንም ለሆድ ይበጃል

2403. ዞርን ስሜነይ ዞድን ስዩነ

. ቢመክሩት የማይመለስ፣ ቢደቁሱትም አይመለስ

.. ሲመክሩት አይመከር በደም ይነከር

2404. ዞርን እጠይ ቀችን ስሜነ

. ቢመክሩት እምቢ ያለ ቢያስሩት አይመለስም

.. ተፈጥሮን ተመክሮ አይመልሰውም

2405. ዞርን እጠይ ዞድ በኤስ

. ቢመክሩት አልሰማ ያለ ጭነት ይሸከማል

.. ምከረው እምቢ ካለ መከራ ይምከረው

2406. ዞርያ ኤኪነ አሰ ከሬን ቀንጥን ዱጤን ምተይ ዶሌስ

. ምክር የማይቀበል ሰው ደጅ ተቆርጦ የማይወድቅ እንጨት ይበቅላል

.. ምክር ያልመለሰው መከራ ደረሰው

2407. ዞሬተይ ጊግን ጭመተይ ናአ ከኤሰ

. ምክክር ሲሰምር የስርቆት ምግብ ሁለቴ ይሰራል

.. አጉል ፍቅር ያመናቅር

2408. ዞኮይ እጥን ኦተይ ገንጇ እጥን ከሌስ

. ጀርባውን እስከሚጐበጥ የሠራ ሆዱ እስከሚያቅተው ድረስ ይጠግባል

.. ሣይሰሩ ማግኘት ሣይፀድቁ ገነት አይገኝም

2409. ዞጥደ እንድዮ ኬችደ አዴ ሃታ ካከፍድ ወዴስ

. የቆረፈደችውን አሮጊት የጠነዛ ሽማግሌ ውሃ አርከፍክፎ ይለብጣታል

.. ቢጤ ቢጤውን ይፈልጋል

## የ

2410. የሸ ኡረይ መችያ ሞይስን ክዩስ

. ፈሪ ሰው በሚስቱ ይታጀባል (ይሸኛል)

.. ፈሪ አይፀድቅም

2411. የሸይ እሻ ሾቤስ

. ፈሪ ወንድሙን ይገላግላል

.. ፈሪ በገዛ ጠቡ ገላጋይ ይሆናል

2412. የሻመይ ቶሊ ሰጢ ኦይቅድ ኡተ ግደ ጌሌስ

. ፈሪ ከፉኛ ነክሶ ይዞ እንሰት ውስጥ ይገባል

.. የነብርን ጅራት አይይዙም ከያዙም አይለቁም

2413. ያ ሰአ ግን ሃ ሰኤስ ከነይ

. ወዲያ ንከስ ሲሉት ወዲህ ይነክሣል ውሻ

.. ፍየሏ ወዲያ ቅዝምዝም ወዲህ

2414. ያ ኼቅን (ቀንግን) ሃ ገኪስ ደውሮ ጦሰይ

. የዳውሮ ውቃቢ ወዲያ ሲረግሙት ወዲህ ይደርሳል

.. ለሰው ልጅ ያሉት ለገዛ ልጅ ይደርሳል

.. ስራ ለሰሪው እሾህ ላጣሪው

2415. ያሸንቸይ በር እሻ ሾቢስ

. ፈሪ ወንድሙን ይገላግላል

.. ፈሪ በገዛ ጠቡ ገላጋይ ይሆናል

2416. ያሬ ገረዋ እክሲያረ ምዜስ

. የሚስገበግብ ድመት ከፀጉር ጋር ይበላል

.. የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሣል

.. የቸኮለች አፍሳ ለቀመች

2417. ያሬት ባርን ጉስስ ዎሬስ

. ተስገብግበው ሲጉርሱ አስቀዝኖ ይገላል

.. አተርፍ ባይ አጉዳይ

.. ስሱ አንድ ያንቀው አንድ ይወድቀው

2418. ያነው ያሎ ዮሼ፣ ስትመጪ ቀንጅት

. ያይቸዳ ዴቦ ዳቴ ከመጣሽ ወዲህ የድምብላል ልንቅጥ

.. በእጅ የያዙት ወርቅ ከመዳብ ይቆጠራል

2419. ያናሽን መልዶ ኀዝዴ፣ የይቸደ ዴቦ ዳቴ

. ከመምጣትሽ በፊት እንደጨሌ የምታምሪ፣ ከመጣሽ በኋላ የድምብላል ልንቅጥ

.. በእጅ የያዙት ወርቅ ከመዳብ ይቆጠራል

2420. ያደ የዮፐ ከሬን ኡቶፐ

. ከመጣሽ አትፍሪ እደጅ አትቀመጭ

.. ከመጣሽ ማርያም ታምጣሽ

2421. ያደ የዮፐ ጌመን ኡቶፐ

. መጥተህ አትፍራ በድብቅ ቦታ አትቀመጥ

.. ቀድሞ ባልዘፈንሽ ከዘፈንሽም ባላፈርሽ

2422. ዩሽ ቆፔነይ ዩይ አቂስ

. አዙሮ የማያስብ ዞሮ ያድራል

.. ያላወቁ አለቁ

2423. ይቲቴ ያነ በልጉዋስ ዋሴስ

. እርኩም ለሚመጣው ክረምት ይጮሃል

.. ሞኝ የእለቱን ብልህ ያመቱን

.. ሆድ ሆዱን የምትል ወፍ አለች ምን አለች፣

2424. ይንዶይ ለይታፔ ያነ በልጉዋስ ዋሴስ ጌቴስ

. እርኩም ለመጪው ክረምት ይጮሃል ይባላል

.. ሞኝ የእለቱን ብልጥ ያመቱን

2425. ዱሎይ አዋ አፎን ዱድድ በው ቦለን አቴስ

. ንዴት ባለቤቱን ገደል ሰድዶ ለራሱ ይቀራል

.. የተከፋ ተደፋ

2426. ዱሞይ በ ቡልያ ደንደይቤናሽን ሰምአለ ጡጋ ማዴስ

. ዱሞ የራሱን እንስራ ሳይችል የሳምአላን ገች ያግዛል

.. አንቃ ለራሱ አይበቃ ለሰው ጠበቃ

2427. ዱባታ ኤሌለውሱ ልቃቃ ሞሞለውሱ

. ያለመጠን ትቸኩላለች ልቃቂት ትጠነጥናለች

.. የቸኮለች አፍሳ ለቀመች

2428. ዱኦቴት ቀንጌተ ኤርሴስ

. የሙት ልጅ መሆን እርግማን ያሳውቃል (ያስተምራል)

.. ችግር ብልሃትን ትፈጥራለች

2429. ዱአይ አሠራረ ሃይቄስ

. አባት እናት የሌለው ልጅ በጥብቆ (ልብስ) ይሞታል

.. አባት የሌለው ልጅ መዝጊያ የሌለው ደጅ

2430. ዱአይ ከልድ ደደው የምበርሻ ኦሌስ

. የሙት ልጅ ሲጠግብ ለነጐድጓድ ወንጭፍ ይወረውራል

.. የቀበጡ ዕለት ሞት አይገኝም

.. አይጥ ለሞቷ የድመት አፍንጫ ታሸታለች

2431. ዱአይ ይሞፑዋ ዴምን ቆመይ ዋይሴስ

. የሙት ልጅ ጅንፎ ሲያገኝ የጦር እንጨት (ዘንግ) ያጣል (ይቸግረዋል)

.. የድሃ ነገር ማንገቻ የለውም

2432. ዱዳ ከውዋ ማነው ቢደ ከውዋ ነሼስ

. የተሾመውን ንጉስ ለመብላት የተሻረውን ያሞግሣል

.. ብልጥ ሰው የሚታወቅበት አይመስለውም

2433. ዑሆይ ዑለው ኢተ

. ለቅሶ አለመድረስ ያሳፍራል

.. አንድ ቀን ቢሳሳቱ አመት ይፀፀቱ

2434. ዑሆፔ እንዴ ቡለች ኬሀ

. ከለቅሶ የአሮጊት ሰርግ ይሻላል

.. ቢያስቀዝንም ጮማ ይሻላል

2435. ዑለ ውርሰ ቦሎትዮ ብሮን ዑልየ ነእያ ሀይ ጎድንቶ እንቴጌ ታጋ መላ ግዴነ ገውሱ

. ወልዳ የጨረሰችውን አማት ገና የምትወልደው ምራት አይ እሜቴ የኔ እንደርስዎ አይደለም ትላለች

.. ልጅ ለናቷ ምጥ አስተማረች

2436. ዑለ ጌና ጋሌ መችያ ዑልን ድቾ ገተ ጌስ

. እሰይ ውለጂ ያሌላት የጋሌ ሚስት ብትወልድ አሳድገሽ አድርሺ ይላል

.. ና ብላ ሣይሉት ከወጡ አውጡልኝ

.. ሳይጠሩት የመጣ ሳይጠግብ ይሄዳል

2437. ዑለናረ ግያ ብን ዑልሰናረ ኬታ ናገውሱ

. የምትወልደው ገበያ ስትሄድ የምታዋልደው ቤት ትጠብቃለች

.. የምጣዱ እያለ የእንቅቡ ተንጣጣ

2438. ዑለው ኬስዶ መሸን እሻ ሾጬቴስ

. ለምንተፍረት ባወጡት ቢለዋ ወንድም ይቆርጡበታል

.. ለሃጥአን የመጣ ለፃድቃን ይተርፋል

2439. ዑለው ኬስዶ ቶረን አዋ ጨድ ዎሬስ

. ለእፍረት ባወጣው ጦር አባቱን ይወጋል ይገላል፣

.. እርሟን ብታፈላ ጋኑን ሙሉ አተላ

2440. ዬለው ዬሎጌ ዙምኬ ጌስ

. ለምንተፍረት የወለዱት አልድህም ይላል

.. ሣይጠሩት የመጣ ሣይጠግብ ይሄዳል

2441. ዬለው ጢንግልያ ቡጣ ኤከውሱ

. ለምንተፍረቷ ጭልፊት ሳር ታነሳለች

.. ሞኝ አያውቁብኝ ባይ

2442. ዬለይ በይና ግድን ዬከ ኤከርከና

. ይሉኝታ ባይኖር ኖሮ አልቅሼ በወጣልኝ

.. ይሉኝታ የራስ አሊን ቤት የፈታ

2443. ዬሎይ አትን ሾለይ ላቴስ

. የተወለደ እያለ የተጠጋ ይወርሳል

.. ይታደሏል እንጂ አይታገሉም

2444.ዬለገ መችያ ዬለገ በዳላ ሜንተውሱ

. ወጣት ሚስት ለጋ በቆሎ ትሰብራለች

.. አጉል ፍቅር ያመናቅር

2445. ዬላ ሚቸይ ዬቂነ

. የሀፍረት ሳቅ ፈገግታ የለውም

.. የሌባ አይነ ደረቅ መልሶ ልብ ያድርቅ

2446. ዬላ ከይሶይ አዋ ጨዴስ

. ሌባ ሲያፍር ባለቤቱን ይወጋል

.. ባለቤት ሲያፍር እንግዳ ይጋብዛል

2447. ዬሉዋ በይራ ጉግያ ጫለይ ጭሜስ

. በእድሜ የሚበልጠውን ልባም ሰው ያታልለዋል

.. ማወቅ መላቅ አለማወቅ መናቅ

2448. ዩሉዋ ዶግዳረ ፓሁዋ ዶገውሱ

. መውለድ የረሳች መጋትም ትረሳለች

.. ተድረው ቢመለሱ የውሃ መንገድ ረሱ

2449. ዩል በይናጌ ጢሪ ባሬስ

. እፍረት የሌለው ጠርጎ ይጕርሳል

.. ይሉኝ አይል የኋላውን አያይ

2450. ዩልየ መቾኔ ዶልያ ገድያኔ ዩዶፐ

. የምትወልድ ሚስትና የሚያበቅል መሬት አትልቀቅ

.. ልጅ ጠልቶ ምን ይወደል ማር ሸጦ ምን ይገዟል

.. የሚስት ወይዘሮ እርሻው ጋራ ዞሮ

2451. ዩልያ ምሽርያ ዴሽን ጤሳ ጎርፐያረ ተው ጤሰይ ዱጤስ ገውሱ

. የምትወልድ ሴት እያለች ወገብ የምታሸው ወገቤ ተበጠሰ ትላላች

.. የምጣዱ እያለ የእንቅቡ ተንጣጣ

2452. ዩልዳረ ዴእሽን ሾልያ ላጨውሱ

. የወለደች እያለች የተንሸዋረረች ትልሣለች

.. አያገባው ገብቶ አያወዛው ተቀብቶ

.. የተኛችው ሳለች ያዳመጠች አረገዘች

2453. ዩልድ ዩገኔ በእድ ዩጠኔ

. ወልዶ ይጥዷል አዝሎ ይዘፍኗል

.. ከአጋም የተጠጋ ቁልቋል ሲያለቅስ ይኖራል

.. ላም እሣት ወለደች እንዳትልሰው ፈጃት እንዳትተወው ልጇ ሆነባት

2454 ዩልድ ዩጊ በእድ ዩጢ?

. ወልዶ ይጥላል አዝሎ ይዘፍናል?

.. ጣት ገማ ተብሎ ተቆርጦ አይጣልም

**2455.** ዬሌተ መለይ ሀይቆ ገለስ በዬስ

. የተፈጥሮ መልክ የሞቱ እለት ይጠፋል

.. ሞት አይቀር ስም አይቀበር

2456. ዬሌቻ ከሎይ ያነ በልጉዋ ኤርሴነ

. የአሬራ ጥጋብ የሚመጣውን ክረምት ያስረሣል

.. ሞኝ የእለቱን ብልጥ ያመቱን

2457. ዬሌነ መችዮ ዎሬነ ሀርግየን ፓጨ

. ያልወለደችን ሚስት በማይገድል በሽታ ታዘባት

.. ጥቂት ታመህ ወዳጅና ጠላትህን ለይ

2558. ዬሌነ ነአይ ዬልዶ ሶሁዋ ጤሌሰ

. ያልወለዱት ልጅ የወለዱበትን ስፍራ ያያል

.. የሰው ልጅ ከማሳደግ የውሻ ልጅ ማሳደግ

2559. ዬሎ ነአይ ዬኪድ ቢድ ሚጪድ ዬስ

. የወለዱት ልጅ እያለቀሰ ሄዶ እየሣቀ ይመጣል

.. የዘመድ ጥል የስጋ ትል

.. ማን እንደራስ ልጅ

2460. ዬሎ ነአይ ዬኪድ ቢድ ዬጢድ ዬስ

. የወለዱት ልጅ ሲያለቅስ ሄዶ እየዘፈነ ይመጣል

.. የዘመድ ጥል የስጋ ትል

2461. ዬሎጋ ዎርድ ሀራ ዬለናው መሮ ሶ ቤቴስ

. የወለዱትን ገድሎ ሌላ ለመውለድ ጠንቋይ ቤት ይሄዳሉ

.. ሰዶ ማሳደድ ካማረህ ዶሮህን በቆቅ ለውጥ

.. ልፋ ያለው በህልሙ ስልቻ ይሸከማል

2462. ዬሎይ ዬዱዋ ድጌነ

. ልጅ መውለድ መፍታትን አያስቀርም

.. ከብዙ ፀሎት የልብ ጥራት

.. አይመጣምን ትተሽ ይመጣልን በጨመርሽ

2463. ዬሎይ ዶጌትን ፓሆይ ዶጌቴስ

. መውለድ ሲረሳ መጋት ይረሳል

.. ተድሮ ቢመለሱ የውሃ መንገድ ረሱ

2464. ዬርሽን እጥዳረ ጎችሽን በውሱ

. ሲስሚት እምቢ ያለች ሲጐትቷት ትሄዳለች

.. ሲስሚት ትታ ሲስቧት

2465. ዬሳምያ ጮረይ መራ ዎሬስ

. የማለቢያ ዕቃ ብዛት ለጥጃ ዐር ነው

.. ሞኝ የዕለቱን ብልህ ያመቱን

.. ሆዱን ያለ ሆዱን ተወጋ

.. ሆዱን የወደደ ማዕረጉን ይጠላል

2466. ዬተይ ሆእን ዶሜ ዱሬስ

. ዘፈን ሲሟሟቅ ዱሽ ይጨፍራል

.. የነገሩ ሁነኛ የጦሩ አርበኛ

2467. ዬቻ ዬጌናረ ምንጣፌ ቁምኤስ ገውሱ

. የኮባ ቅጠል የማታነጥፍ ምንጣፍ ይቆረቁራል ትላለች

.. አህያ የሌላት በቅሎ ትንቃለች

2468. ዬችያ ፑዴተን ቶጌነ ፐረይ ዬቻ ማዮ

. በዬቺያ ዳገት ላይ የማይቀመጡበት ፈረስ ቅጠል ይልበስ

.. ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ

2469. ዬከና አይፍየን ዴሬቆፐ

. በምታለቅስበት አይን አታፍጥበት

.. እዩኝ እዩኝ ያለች ደብቁኝ ደብቁኝ ትላለች

2470. ዬዶ ኢተይ ጎምየን ገቴስ

. ክፉ ግልቢያ መአት ላይ ይጥላል

.. አለማረፍ ጣር ያበዛል

2471. ዬዶ ድገ ሜቶቶፐ፣ ቦከ ሆአ ሜጊቶፐ

. ፈተህ ለቀህ አትቸገር፣ ጭረህ ሙቀህ አትበረድ

.. ሣይርቅ በቅርቡ ሣይደርቅ በርጥቡ

2472. ዬዳ ደሮይ ባዘን ኬሴስ

. እጅግ መጋለብ ከጠላት ጋር ያጋጥማል

.. እጅግ ብልሀት ያደርሳል ከሞት

2473. ዬዴነን ዬሰ፣ መንቄነን ዱሬተ

. ፈተህ ሣትለቅ እለብ፣ ድህነት ሣይደርስብህ ክበር

.. በጊዜው ስራበት

2474. ዬገነው አይሰ ቁማ አገናው ቦሎ ከነ

. እንዳይጣል የቅቤ ምግብ እንዳይተው የአማች ውሻ

.. ላም እሳት ወለደች እንዳትልሰው ፈጃት እንዳትተወው ልጇ ሆነባት

2475. ዮሁዋ ሌምሶይ ቆሄስ

. ነገርን ተረት ያለዝበዋል (ያረግበዋል)

.. ነገር በምሣሌ ጠጅ በብርሌ

2476. ዮሁዋዮ ቀሾይ ሰአዮ ቀመይ ጌቴስ

. ለነገር መደምደሚያ ለቀኑ መምሸት ይባላል

.. ነገር ቢበዛ ባህያ አይጫንም

2477. ዮሁዋ ኤርየ ብተኔ ዴርያ በሼስ

. ነገረኛ ሰው አገር ያበላሻል

.. በጥባጭ ካለ ጥሩ ውሃ አይጠጣም

2478. ዮሁዋ ኮይየ ከንያ ባዶ ከርየን ህይቀውሱ

. ነገር የምትፈልግ ውሻ ሄዳ ከጥለኛ ሰው ደጅ ትሞታለች

.. ነገረኛ ሰው ከቤቱ አይሞትም

.. እንኳን ዘንቦብሽ ቀድሞም ጤዛ ነሽ

2479. ዮሁዋ ዛርየይ በይራ – ነገር የሚቋጭ ሽማግሌ

ኬታ ዛርየይ ዎይሻ– ጣሪያ የሚቋጭ ቀርከሃ

ኮሻ ዛርየይ መዝያ– ረሃብ የሚያስታግስ እንሰት

.. ሽማግሌ ይገላግላል የተጠቃ አቤት ይላል

2480. ዮሁዋፔ ቱመይ ሎኦ (ኬሃ)

. ከነገር ውስጥ እውነት ጥሩ ነው

.. እውነት ተናግሮ ከመሸበት ማደር

2481. ዮሆ አዱስ ሀሬ ጫን ኤሬነ

. የነገር ረዥም አህያ አይጭንም

.. ነገር ቢበዛ በአህያ አይጫንም

2482. ዮሆ ውርስደይ ቪምፔስ

. ነገሩን (ጉዳዩን) የጨረሰ ያርፋል

.. ነገር አለኝ ከማለት ስራ አለኝ ማለት

2483. ዮሆን ጨድየ ኡራፔ ቶረን ጨድያጌ ኬሀ

. በነገር ከሚወጋ ሰው በጦር የሚወጋ ይሻላል

.. በነገር ከወጉበት በጦር የወጉበት ይድናል

2484. ዮሆይ ደ[illegible]ድ ሀርየን ጫኔቴነ

. ነገር ቢበዛ ባህያ አይጫንም

.. ነገር ቢበዛ ባህያ አይጫንም

.. ከሺ ቃላት አንድ ጋት ስራ

2485. ዮረይ መልኡዋ ኤሬነ

. ሆዳም ሰው ጣእምን አያውቅም

.. አፈሰፌ ሰው የምግብ ጣእም አያውቅም

.. ሆዳም ፍቅር አያውቅም

2486. ዮቀይ በር ሚዜ አሹዋፔ አቴስ

. ሞኝ ከላሙ ስጋ ሳያገኝ ይቀራል

.. ሞኝ አሳላፊ ወንድሙን ይጎዳል

2487.ዮቅ ዮሆ ዶጌን፣ ናችሳ ፐርሶይ ጪሞ አጌነ

. ሞኝ ነገር አይረሳም፣ ለጋ ቦርዴ መምረሩ አይቀርም

.. ሞኝና ወረቀት የያዘውን አይለቅም

2488. ዮት ገትኮ ዮሆይ ኤሬቴስ

. ተናግረው ዳር ካደረሱ ውጤቱ ይታወቃል

.. ነገር ከሥሩ ውሃ ከጥሩ

2489. ዮትድ ሱቆ ሱቆይ ጥንቄነ

. ተናግረው የፈሱት ፈስ አይገማም

.. ተማክረው የፈሱት ፈስ አይገማም

2490. ዮአንችያ ሃታ ጮመ ምተውሱ

. ነገረኛ ሴት ውሃ አኝካ ትውጣለች

.. ነገረኛ ዝንዠሮ ውሻ ታረባለች

2491. ደልቦ አቦ እንተ ነአ አይስ ግየን ወዴት? ግን ግያፔ
አክያሰአን አውን ወዶ ጌስ

. የደልቦ አባት ልጅዎን እንዴት እገበያ መሃል ይደበድቡታል? ቢባል ከገበያ የሰፋ የት ወስጄ ልደብድበው ይላሉ

.. ሀራምባና ቆቦ

2492. ደልቦ ከውከይ ደንገርሳ ዎርን መልዲጬ ከውከይ ማዩዋ
ሃድርስ ቁማዬስ

. የዳልቦ ንጉሥ ዝሆን ቢገድል የመልዲጬ ንጉስ ልብሱን በግራ ትከሻው ያጣፋል

.. በሰበቡ መምሬ ተሳቡ

2493. ደምበላ... ሚዶባንኔ ኡይዶበን ዶጬ... ቡቻ ሜዶቴስ

. የዳምበላ ሸክላ ሰሪ በበላበትና በጠጣበት የዶጮ ሸክላ ሰሪ ፂሙን ይላጫል

.. አይጥ በበላ ዳዋ ተመታ

2494. ደረቾ ጎዳ ሄረኖይ ጋሞ ጉልቴፔ በነ ቀሽስየ ዎረቃታ
ኤሄስ ግዮጋደን

. የደረቾ (ፈረስ) ጌታ ሄረኖ (ስም) ከጋሞ ጉልታ (ቦታ) ራሱን የሚያሳስር ወረቀት ያመጣል እንደሚባለው

.. ያወቀ ዘለቀ ያላወቀ አለቀ

2495. ደረነ ደቦይ ደረን ያእን ጉጠነይ ጉተራ ክዬስ

. ገመናውን የሚጠብቅ ዘመድ በጫካ ውስጥ ሲመካከር ገመናውን የማይደብቅ አደባባይ ይወጣል

.. የማያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል

2496. ደርኮን አይችን ደውሮን ጌለውሱ

. ጐረቤት የታጨች ዳውሮ አገር ሄዳ ታገባለች

.. ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ

.. ምኞትና ጉም አይጨበጥም

2497. ደሪ ለሌሴትየይ ላፈ ጌሌስ

. ምርጫ የሚያበዛ ሰው የማይረባ ሰው ያገባል

.. መራጭ ይወድቃል ከምራጭ

2498. ደሪ ዛሰይ ላፈ ጌሌስ

. ብዙ የሚንጠራራ የማይረባ ያገባል

.. መራጭ ይወድቃል ከምራጭ

2499. ደሪ ጉሪን ደርኮን ዎንቴስ

. በጣም ማለድኩ ሲባል ከጓሮ ይነጋል

.. የሩቅ አላሚ የቅርብ አዳሪ

2500. ደሪንቻ ኦተይ ደውለን መኬስ

. ጓሮውን ያለማ በዳውላ ይሰፍራል

.. ግንበኞች የናቁት ድንጋይ የማዘን ራስ ሆነ

.. የናቁት ያስረግዛል

2501. ደሮ ማነ ግየይ ደቦቼ አቴስ

. ብዙ እበላለሁ ያለ ከዘመድ ይቀራል

.. ብቻውን የበላ ብቻውን ይሞታል

2502. ደሮ ዳነ ቬምቱዋ ጐሜ ዎሬ

. ብዙ የሚቆየውን ነፍስ ግፍ ይገላል

.. ችኩል እግር ከዘንዶ ጉድጓድ ይገባል

2503. ደሮቼ ኮይን ከይሶይ አልኤስ

. ለቁም ነገር ሲፈልጉት ሌባም ይወደዳል

.. ለመድሃኒት ካሉ ድምብላል ይወደዳል

2504. ደቡዋ ላፈይ አቡዋ ፐይዴስ፣ ሚዛ ላፈይ ቶጎጉዋ ፐይዴስ

. ትንሽ ዘመድ ያለው አጎት ይቆጥራል

ጥቂት ላም ያለው ማለቢያ ጮጮ ይቆጥራል

.. ትንሽ ያላት እንቅልፍ የላት

2505. ደቡዋ ደገተይ ጠልያ ኡሼነ

. ብዙ ዘመድ መኖር ኮሶ አያስጠጣም

.. ዘመደ ብዙ ጠላዋ ቀጭን ነው

2506. ደቦ ግን ዱቡሽን ሞቴስ፣ መልኦ ግን ባጭረይ ጨሌስ

. ዘመድ ነው ሲባል በአደባባይ ይሞግታል

.. «ባጭራ» ጣፋጭ ነው ሲባል ያንቃል

.. የዘመድ አዳይ ጦም ያሳድራል

2507. ደቦ ግን ዱቡሽን ሞቴስ፣ ሹጎ ግን ባጭረይ ጨሌስ

. ዘመድ ነው እየተባለ በአደባባይ ይከሳል፣ ለስላሳ ነው እያሉ
ጭብጦ (ከቆጮ የሚሠራ) ያንቃል

.. ያመኑት ፈረስ በደንደስ

.. ምቀኛ ከቤት ይወጣል

2508. ደቦተይኔ ዜሬተይኔ ከቅ ዎትን ኪሀ

. ዝምድናና ዘር ቋጥረው ቢያስቀምጡት ይሻላል

.. ለወዳጅና ለአይን ትንሽ ይበቃል

2509. ደቦቴታ ደሮይ በቀ ኦይሳ ተልእሴስ

. የዝምድና ብዛት የጨሌ ቅቤ ያበዳድራል

.. ፍቅር ሲጠና ቆሎ ያጓርሳል

2510. ደቦን ፖኮ አሰ ቤአናፔ ሃርየን ቦሮቆ ቤአነ

. በዘመድ ነውር ከማየት የአህያ ቦቃ ማየት ይሻላል

.. ሞኝ ባያፍር የሞኝ ዘመድ ያፍር

2511. ደቦይ በይነ እስኔ ካሽ በይነ ኬተይኔ እሱዋ

. ዘመድ የሌለው ሰውና ታዛ (ሰበሰብ) የሌለው ቤት አንድ ነው

.. ወገን ብዙ ሰው ማንም አይታገለው

2512. ደቦይ ደቦኮ ግን ቶጎጎይ ሚዘ አቆ ዎጤሰ

. ዘመድ ወደ ዘመድህ ቢባል ጮጮ ወደ በረት ይሮጣል

.. እየወገንህ ቢሉት የመቶ አመት ቆዳ ከብት ተራ ቆመ

2513. ደንክዮጋኔ ዶጎፐ ደንኬትዮኔ አጎፐ

. መጨበጡንም አትተው መሰብሰቡንም (መብላቱንም) አትርሳ

.. ሁለት ጉድጓድ ያላት አይጥ አትሞትም

2514. ደንኪ አዬስ ደቦይ ደሮ

. ለጋስ ሰው ብዙ ዘመድ አለው

.. ዘመድ ብዙ ጠላዋ ቀጭን ነው

2515. ደንዳየይ ደሬስ

. የቻለ ይከበራል

.. መከራን የቻለ አሸናፊ ነው

2516. ደንደይደይ ከዎ ጌሌስ

. የታገሰች ንጉስ ታገባለች

.. መከራን የቻለ አሸናፊ ነው

2517. ደንደይደይ ደሬስ፣ ደርደይ ዳነቴስ

. የቻለ ትልቅ ይሆናል፣ ትልቁ ደግሞ ይሾማል/ዳኛ ይሆናል

.. መከራን የቻለ አሸናፊ ይሆናል

2518. ደንገርሰይ ግተ ግን ኤጩ.ያ ላ ኑሶ ዲዲሞንተ ኬኔሽ ገውሱ ጌቴስ

. ዝሆን ትልቅ ነው ቢሏት አይጥ አንተ የኛን ቤት እንዲዲሞን ያህል ይሆን አለች ይባላል

.. አባይን ያላየ ምንጭ ያመሰግናል